# የወያኔ የማስመሰያ ‹‹ሕገ መንግሥት›› (façade constitution) ፤ በማር የተለወሰ እሬት

ከይኄይስ እውነቱ

ይህንን ጽሑፍ ለማቅረብ ያነሳሳኝ የወያኔ አገዛዝ ከተወገደ በኋላ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ስንናፍቀውና ስንመኘው ለቆየነው በሕግ የበላይነት ላይ የሚመሠርት የእኩልነትና የዲሞክራሲ ሥርዓት መሠረት የሚሆን አዲስ ሕገ መንግሥት ያስፈልገናል? ወይስ ወያኔ ሆን ብሎ ከፋፍሎ ለመግዛት እንዲያመቸውና የጎሣ/ጥላቻ ፖለቲካ ለማራመድ፣ የአገሪቱን አንድነትና ግዛት ሉዐላዊነት ለመፈታተን፣ በጓዳ ያዘጋጀውን ‹ሕገ መንግሥት› ይዘን እንቀጥል የሚለው ርእሰ ጉዳይ በተቃዋሚዎች፣ በምሁራን፣ በሲቪክ ተቋማት እና የአገራቸው ጉዳይ በሚያሳስባቸው ዜጎች ዘንድ (ለጉዳዩ በሚመጥን ደረጃ ባይሆንም) መወያያ በመሆኑ ነው፡፡

የወያኔ አገዛዝ ለሕግ የማይገዛ/የሕግ የበላይነትን የማይቀበል መሆኑን ለዓመታት በተግባር ያስመሰከረ፣ ከሽፍትነት አስተሳሰብ ያልተላቀቀ የጥቂት ወንበዴዎች ስብስብ መሆኑ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ አገዛዙ ራሱ አዘጋጅቶ ራሱ ያፀደቀውን ‹ሰነድ› ለሥልጣኑ/ለህልውናው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ብቻ፣ ለአሳዳሪዎቹ ነጮች ማስመሰያ እንዲሁም ‹ለድብቅ አጀንዳው› በመጠባበቂያነት ከሚጠቀምበት በስተቀር በዚህ አገዛዝ በተግባር ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት የሚባል ነገር ጨርሶ የለም፡፡ ለዚህም ይመስላል በርካታ ምሁራን የወያኔን ‹ሕገ መንግሥት› የተጻፈበትን ወረቀትና ቀለም ያህል ዋጋ የለውም በማለት የሚናገሩት፡፡ ያም ሆኖ ወያኔ በ‹ሰነዱ› ላይ የማሻሻያ አሳብ ሲነሳ ምን ሲደረግ በመቃብሬ ላይ እንጂ በማለት ይደነፋል፡፡ የእኔም ትኩረት ወያኔን ወደ ታሪክ ቆሻሻ ቅርጫት ካስወገድን በኋላ በነፃነት ማግስት ስለሚያስፈልገን ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት ይሆናል፡፡

ከተለያዩት የብዙኃን መገናኛዎች የምናገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ የአገዛዙን ተቃዋሚዎች - የፖለቲካ ማኅበራት (በግልጽ በፕሮግራማቸው ሠፍሮ ባናገኝም) ፣ ሲቪክ ማኅበራት፣ ምሁራን፣ ግለሰብ ዜጎች - አቋም ስንቃኝ የሚከተለውን መታዘብ እንችላለን፡፡

ሀ/ አንደኛው ወገን የወያኔን ‹ሕገ መንግሥት› መሠረታዊ ችግር ተግባራዊ አለመሆኑ ላይ አሥምሮ ማሻሻያ በማድረግ መጠቀም ይቻላል የሚለው ነው፡፡

ለ/ በዋናነት በጎሣ በተደራጁ ፖለቲከኞች የሚራመድ አቋም ሲሆን የወያኔን ‹ሕገ መንግሥት› ይዘን መቀጠል እንችላለን የሚለው ነው፡፡

ሐ/ ሌሎች ደግሞ የአገዛዙ ‹ሕገ መንግሥት› መለወጥ እንዳለበት በይፋ ሲናገሩ ይሰማሉ፤ ሆኖም ትክክለኛ ፍላጎትና አቋማቸው ሲፈተሽ አዲስ ሊያዘጋጁ የሚያስቡት ‹ሰነድ› ከወያኔ መሠረታዊ ልዩነት የሌለው እንደሆነ ንግግራቸውና መግለጫቸው ያሳብቃል፡፡

መ/ የወያኔ ‹ሕገ መንግሥት› ሙሉ በሙሉ መለወጥ ይኖርበታል ብለው የሚያምኑ ናቸው፡፡

ከዚህ ቀደም ባቀረብኳቸው አስተያየቶች ደጋግሜ እንደገለጽኩት ለእኔ ‹መንግሥት› እና ‹ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት› የምንላቸው ‹ተቋማት› ለወያኔ/ሕወሐት ባሕርይ አይስማሙም፡፡

በእኔ አስተሳሰብ ከወያኔ አገዛዝ በኋላ ለምናስባትና ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት እንዲኖርባት ለምንፈልጋት ኢትዮጵያ የሚመጥን አዲስ ሕገ መንግሥት ያስፈልገናል፡፡ ወደ ዝርዝር ጉዳይ መግባት በጣም አካዳሚያዊ ስለሚሆንብኝ የወያኔ ‹‹ሕገ መንግሥት›› መለወጥ የሚያስፈልግበትን ጎላ ጎላ ያሉት ምክንያቶች አለፍ አለፍ እያልኩ ለማንሳት እሞክራለሁ፡፡

1. ሕጋዊም ሆነ ፖለቲካዊ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ (question of legitimacy)
አንድ ሕገ መንግሥት ዓለም ለተቀበለው ግን በተግባር ለማይውል የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች እውቅና መስጠቱ ብቻ ሰነዱን ተቀባይነት (legitimacy) ያለው አያደርገውም። የዲሞክራሲ ሥርዓት ለመሥፈኑም በየትኛውም መመዘኛ ማረጋገጫ/ዋስትና ሊሆን አይችልም። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሌለበት የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አይከበሩምና። የወንበዴው ሕወሐት አገዛዝ ከሕግ በላይ በመሆን በራሱ ‹ሕገ መንግሥት› የተካተቱ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን በሙሉ በመተላለፍ ‹እጆቹን› በንጹሐን ደም ያረከሰ ፋሺስታዊ ቡድን ነው። ይህም በጊዜው ጊዜ ከበቂ በላይ በሆነ ማስረጃ የሚረጋገጥ ይሆናል።

አንድ ሕገ መንግሥት ከዝግጅቱ (ከማርቀቁ ሂደት) እስከ ይዘቱ ፤ ሕዝብ ሰነዱን በማዳበርም ሆነ በማፅደቁ ሥርዓት ያለፈበት ሂደት፤ በየጊዜው ሊሻሻል፣ የበለ ሊጠራና ውጤታማ ሊሆን የሚችል ዘላቂነት ያለው ሥርዓትና ተቋማት የማስገኘት ውጤቱ፤ የሚተዳደርበት ሕዝብ ያለውን ኅብረት፣ አንድነት፣ መተሳሰብ የሚያጠናክሩ ለዘመናት የዘለቁና የጋራ የሆኑ ባህላዊ፣ታሪካዊና ትውፊታዊ እሤቶች ማንፀባረቁ፤ ባቋቋማቸው የመንግሥት ሥልጣን አካላት መካከል ያለው የርስ በርስ ቊጥጥር/ምዝዝን ሥርዓት፤ ገዢውም ተገዢውም ሰነዱ ጥበቃ ለሚያደርግላቸው መርሆዎች ያላቸው ታማኝነትና አክብሮት፤ ወዘተረፈ ግምት ውስጥ በማስገባት ኹለንተናዊ (holistic) በሆነ መልኩ ማየትን ይጠይቃል።

ለአንድ ሕገ መንግሥት ሕጋዊም ሆነ ፖለቲካዊ ተቀባይነት እንደማሳያ የሚወሰዱ የተለያዩ መለኪያዎች መኖራቸውን በጉዳዩ ላይ የተጻፉ የምሁራን ሥራዎች ቢያመለክቱም ፅንሰ ሃሳቡ በሚገባ ፍቺ ያልተሰጠውና በበቂ ንድፈ ሃሳብ ያልተደገፈ እንደሆነ ሥነ ጽሑፎች ያመለክታሉ። በዚህም ምክንያት እንደሚያራምዱት ንድፈ ሃሳብ ለሕገ መንግሥት ተቀባይነት መመዘኛ የሚያደርጓቸው ነጥቦችም የተለያዩ ናቸው። ለዚህ አስተያየት ዓላማ ጠቅለል ያሉ መመዘኛዎች ላይ እናተኩራለን።

- የአገር መተዳደሪያ መሠረታዊ ሰነድ እንደመሆኑ አብዛኛው ሕዝብ ተሳትፎ ያደረገበት መሆኑ፤ ስምምነቱንም (የአፀዳደቁ ሂደት) በዲሞክራሲያዊ ሥነሥርዓት የገለጸ መሆኑ፤ይህንንም ለማስፈጸም የሚቋቋሙ ተቋማት የሕዝብ ፈቃድ ያለባቸው፣ በአሠራራቸውም ነፃነት፣ ገለልተኝነት እንዲሁም ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለባቸው መሆኑ፤
- በሥፋት የምንጋራቸውን መርሆዎችና እንዲሳኩልን የምንፈልጋቸውን መልካም ምኞቶች (ideals) የያዘ ሰነድ ነው ወይ?
- የአንድ ሕገ መንግሥት ተቀባይነት ባስከተለውም ውጤት ይመዘናል። በዚህ ረገድ የወረበሎቹ የሕወሐት ሥርዓት ‹መንግሥት› ተብሎ ለመጠራት ባይበቃም፣ የኢትዮጵያን መንግሥት የሥልጣን መንበር በጉልበት ተቆናጦ፣ እገዛዋለኹ የሚለው ሕዝብ/ዜጋ የሚያነሳቸውን ሕጋዊ ጥያቄዎች በሙሉ በብረትና ቅጥ ባጣ ጭካኔ በማፈን፣ ከሕዝብ ፈቃድ ውጭ ለ25 ዓመታት ቆይቷል። ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የሚፈልገው ለማይጠረቃ ሥልጣኑና ዝርፊያው ብቻ ሲሆን፣ አሁን ካደረሰባት ውርደትም በባሰ ወደ በርባሮስ ቢሰዳትም ምኞቱ ነው። ወያኔ በአገርና ሕዝብ አጥፊነቱ

በ21ኛው ክ/ዘመን ከጀመርኑ ናዚና ከጣልያኑ ፋሺስት ጋር በአቻነት የሚታይ ሥርዓት ለመሆን በቅቷል፡፡

በዚህ መለኪያ ስናየው ***የወያኔ ‹ሕገ መንግሥት› ዴሞክራሲያዊ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡*** ‹‹የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚሽን››፣ ‹‹የሕገ መንግሥት ጉባኤ››፣ ‹‹ሕዝበ ውሳኔ›› የተባሉት የይስሙላ ሂደቶች ልክ ወያኔ ‹መቶ በመቶ› አሸንፌአለሁ እንዳለው ‹ምርጫው› የተቀነባበረ ትርኢት መሆኑን አደባባይ ያወቀው ፀሐይ የሞቀው እውነት ነውና፡፡

2. ለሥልጣን ገደብ/ልጓም የማያበጅ መሆኑ

እንደሚታወቀው ***ሥልጣኑ የተገደበ መንግሥት መኖር የሕገ መንግሥት ተቀዳሚና ዋና ዓላማ እንዲሁም ሕገ መንግሥታዊ መርህ ነው፡፡*** ሕወሐት በ‹ፓርላሜንታዊ ሥርዓት› እና ‹ኢሕአዴግ› አዊ ሽፋን የዕድሜ ልክ ገዥ ለመሆን ያለመበትን ‹ሕገ መንግሥት› ተክሏል፡፡ በዚህም የአንድ ፓርቲን ፈላጭ ቆራጭነት በማንገሥ ሕጋዊ የሥልጣን ሽግግር እንዳይኖር በሩን ከመዝጋቱ በተጨማሪ የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት በጽሑፍም በተግባርም እውቅና ነስቷል፡፡ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ሕዝብ ለመሆኑ እውቅና ላልሰጠ፣ የሥልጣን ገደብ ላላበጀ እና ሕዝብ በፈለገ ጊዜ ሊቀይረው የማይችለው ሥርዓትን ያቋቋመ ‹ሕገ መንግሥት› በየትኛውም መመዘኛ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡

3. በሦስቱ የመንግሥት የሥልጣን ዘርፎች መካከል የሥልጣን ክፍፍል መርህ እና የርስ በርስ ቁጥጥርና ምዝዝን ሥርዓት አለመኖር

የወያኔ ‹ሕገ መንግሥት› በሕግ አውጭው፣ በሕግ ተርጓሚው እና በሕግ አስፈጻሚው አካላት መካከል ግልጽ ክፍፍል የማያደርግ ከመሆኑም በላይ የሶሻሊዝምን ሥርዓት ፍልስምና (ሕወሐታዊ ‹አብዮታዊ ዴሞክራሲ›) መሠረት በማድረግ ሕግ አውጪውን (ፓርላማውን/ ‹የተወካዮች ም/ቤት›) የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል መሆኑን በአንቀጽ 50/3 ደንግጓል፡፡ አንዱ የሥልጣን አካል ከሌላው የሚልቅበት ሁኔታ በመካከላቸው ሊኖረው የሚችለውን የርስ በርስ ቁጥጥርና ምዝዝን ሥርዓት የሚያፋልስ ይሆናል፡፡ (ለአብነት ተራ ቍጥር 4ን ይመልከቱ፡፡) በዚህም ‹ሕገ መንግሥቱ› የሥልጣን ክፍፍልን ሳይሆን የሥልጣን አንድነትን በማራመድ ለገዢዎቹ የ‹ኮሚዩኒስት ደቀመዛሙርት› አምባገነንነት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በሕወሐት አገዛዝ በተግባር ሕግ አውጭው አካል የሚኒስትሮች ም/ቤት (ሕግ አስፈጻሚው) ሲሆን የፓርላማው መደበኛ ሥራ ያለቀለት የሕግ ሰነድ ላይ ማኅተም ማሳረፍ መሆኑን ላለፉት 25 ዓመታት የታዘብነው ሐቅ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ‹ሕገ መንግሥቱ› ከዳኝነት ነፃነት ጋር በተያያዘ ስለ ዳኞች አሰያየም፣ ስለሚነሱበት ሁኔታ፣ ዝውውር፣ ዲስፕሊናዊ ርምጃና የመሳሰሉትን በሚመለከት ዋስትና የሚሰጥ ሕገ መንግሥታዊ አካል አልደነገገም፡፡ በተግባር ስናይ ደግሞ ሕግ አስፈጻሚው አካል በዳኝነት ሥርዓቱ (ሕግ ተርጓሚው) ውስጥ እንደፈለገ ጣልቃ በመግባት የአንድ መንግሥት ዓምድ የሆነውን የፍትሕ አስተዳደር ሥርዓት ከሥሩ አናግቷል፡፡ በዚህም የሕግ የበላይነት አለመኖር የወንበዴው ሥርዓት ዓይነተኛ መገለጫ ሆኗል፡፡

4. *ሕገ መንግሥታዊ ጥያቄን የሚያይ የዳኝነት ሥርዓት አለመኖሩ* (Absence of Judicial Review System of Constitutionality) (አንቀጽ 62/1)

*በዓለም ሥራ ላይ ከዋሉ ሕግጋተ መንግሥት ባፈነገጠ መልኩ ሕግ አውጭው የሚያወጣቸው የበታች ሕጎች፣ ሕግ አስፈጻሚው የሚያከናውናቸው ተግባራትና የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች፣ ሕግ ተርጓሚው የሚሰጠው ዳኝነት ከሕገ መንግሥት ጋር ያላቸውን መጣጣም/ሕገመንግሥታዊነትን መርምሮ ውሳኔ የሚሰጠው የአገሪቱ የመጨረሻው ፍርድ ቤት ወይም ለዚሁ ዓላማ የተቋቋመ ሕገ መንግሥታዊ ፍ/ቤት ሳይሆን* ***ፓርላማው (ሕግ አውጭው)*** *መሆኑ ማንም በራሱ ጉዳይ ዳኛ መሆን አይገባውም የሚለውን መሠረታዊ የሕግ መርህ የሚቃረን ነው፡፡ በመሆኑም በሕግ አውጭው፣ በሕግ ተርጓሚው እና በሕግ አስፈጻሚው መካከል ሊኖር የሚገባውን የርስ በርስ ቁጥጥር/ምዝዝን ሥርዓት አፋልሷል፡፡ በዚህም ብቸኛው ገዥ ፓርቲ የሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን ትርጓሜ ለራሱ ፖለቲካ መጠቀሚያ አደርጎታል፡፡*

5. *ኢትዮጵያን ባለቤት ያሳጣት መሆኑ* (*የመግቢያው አንቀጽ*)

*ከመግቢያ አንቀጹ* (preamble clause) *ጀምሮ* (*በዓለም ዙሪያ ፌዴራላዊም ሆነ አሐዳዊ ሥርዓት ባላቸው አገሮች ሕግጋተ መንግሥት ባልተለመደ መልኩ*) *ለአገሩ ባለቤት የኢትዮጵያ ሕዝብ እውቅና ያልሰጠ መሆኑ፤ ‹እኛ› ማነን የሚለውን ጥያቄ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከማለት ይልቅ ‹‹…ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች…›› በማለት የጎሣ አፓርታይድ ሥርዓት በመፍጠር ኢትዮጵያዊ ማንነትን ወደ ጎሣ ደረጃ ዝቅ ያደረገ ሰነድ መሆኑ፡፡*

*ለአብነት ያህል ፌዴራላዊ ሥርዓት የሚከተሉ አገሮች* (*አንዳንዶቹ የያዟቸው ጎሣዎች ስብጥር ከኢትዮጵያም እጅግ የበዛ*) *ሕግጋተ መንግሥት መግቢያ አንቀጾችን ከዚህ በታች አቀርባለኹ፡፡*

- ❖ Constitution of the Federal Republic of Nigeria 1999: ***"We, the people of the Federal Republic of Nigeria…"***
- ❖ Constitution of the Republic of Sudan 2005: "*We, the people of Sudan,…"*
- ❖ The Constitution of the Republic of South Africa 1996: ***"We, the people of South Africa …"***
- ❖ Constitution of the Federative Republic of Brazil1988: ***"We, the representatives of the Brazilian People, …"***
- ❖ Constitution of the Bolivarian Republic of Venezuela: ***"The people of Venezuela,.."***
- ❖ The Constitution of India 1949 (as amended): ***"WE, THE PEOPLE OF INDIA,…"***
- ❖ Basic Law of the Federal Republic of Germany, 2014: ***"…THE German people …"***
- ❖ The Constitution of the United States of America: ***"We the People of the United States, …"***

6. *አወዛጋቢው የመገንጠል ‹መብት› የሚሰጠው ድንጋጌ* (*አንቀጽ* 39)

አንድ አገር የግዛት ክፍሉን/አባሉን - ካንድነቱ ወጥቶ - በፈለገ ጊዜ እንዲገነጠል/‹ፍቺ እንዲፈጽም› የሚያስችለውን ‹ሕገ መንግሥታዊ› ድንጋጌ አስቀምጦ ከቶዉንም ሉዐላዊ ነኝ ማለት ይቻለዋል? የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገዛዞች ያልተበደለበት ጊዜ የለም፡፡ ሆኖም ጎሣን መሠረት አድርጎ ግፍና ጭቆና የተፈጸመው በዘረኛው ወያኔ ብቻ ነው፡፡ ለሁሉም የሚበጀው መፍትሄ በቊጥር ለላቀውም ላነሰውም ዜጋ (የጎሣ ማንነት፣ የሚከተለው እምነት፣ የፖለቲካ አመለካከት ወዘተረፈ ግምት ውስጥ ሳይገባ) መብትና ግዴታውን በእኩልነት የሚያስተናግድና የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት ባንድ አገር ጥላ ሥር መፍጠር እንጂ የተበደለ፣ የተገፋ፣ የተቀየመ፣ ያኮረፈ፣ ባጠቃላይ የተቃዋሚ ሁሉ ዕጣ ፈንታ ከአገራዊው አንድነት መለየት ከሆነ ዛሬ በዓለም ላይ የምናያቸው ሉዐላዊ አገራት ባልኖሩ ነበር፡፡ መለየት/መገንጠል ኃላፊነት የማይሰማቸው፣ የግል ጥቅማቸውን በሕዝብ ስም ለማሳካት ወይም የባዕዳን ተልእኮ አስፈጻሚ መሣሪያ በመሆን የሚያቀነቅኑት መርዘኛ አስተሳሰብ እንጂ በምንገኝበት ዘመን የሕዝብ ምርጫና ፍላጎት ሆኖ አይታይም፡፡ መገንጠልን አጥብቀን የምንቃወመው በሚያስከትለው ደም መፋሰስ ብቻ ሳይሆን በ‹ነፃነት› ማግስትም ለሁለቱም ወገኖች ዘለቄታዊ ሰላምን የሚያስገኝ ባለመሆኑ ነው፡፡

እስከማውቀው ድረስ አሁን በምንገኝበት 21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንዲህ ዓይነቱ የአገርን አንድነት የሚያናጋ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ያላቸው አገሮች ያሉ አይመስለኝም፡፡ ወያኔ ፣መገንጠልን ዋና አጀንዳቸው ያደረጉ ኃይሎች እና የኢትዮጵያን ማኅበረ ኢኮኖሚያው፣ታሪካዊና ባህላዊ ዓውድ ሳይረዱ በጥራዝ ነጠቅነት ባነበቡዋቸው የሶሻሊዝም ሥነ ጽሑፎች የተሳከሩና ለገንጣዮች መሣሪያ የሆኑ ወገኖች የሚያነሱት ስንኩል ሃሳብ ነው፡፡ በዋናነት በዳያስጶራው የሚገኙ የኦሮሞ ምሁራን/ልሂቃን ተብዬዎች ሌላውን ኢትዮጵያዊ በማግለል የሚያካሂዱት ‹‹የኦሮሞ እንቅስቃሴ›› ዐቢይ ዓላማ መገንጠል መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ ይህ የልሂቃኑ ፍላጎት በምድር ላይ መከራውን የሚያየውና ከወያኔ ጋር የሞት ሽረት ትግል እያደረገ ያለው ኢትዮጵያዊ ኦሮሞ ጥያቄና ፍላጎት ነው ወይ ለሚለው አዎንታዊ መልስ ለማግኘት ማረጋገጫ የለም፡፡ የአሁኑን ጨምሮ ባለፉት ሥርዓቶች ኢትዮጵያ ውስጥ በደል ጭቆና የነበረና ያለ መሆኑን ጥያቄ ውስጥ አይገባም፡፡ ልቦለዳዊ ‹‹የውስጥ ቅኝ ግዛት›› የተባለ አስተሳሰብ በመፍጠር የኦሮሞ ምሁራን/ልሂቃን ነን በሚሉቱ ዘንድ ብሔራዊ አንድነት፣ ብሔራዊ ማንነት የለም በሚል ከኢትዮጵያ ለመለየት በጓዳ የሚደረገው ሽርጉድ ለተበደለው/ጭቆና ላንገፈገፈውና ከቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር በጋራ ታሪክ፣ ትውፊት፣ ሃይማኖት፣ ባህል ወዘተረፈ ለተሰናሰለው የኦሮሞ ኅብረተሰብ በጭራሽ መፍትሄ ሊሆን አይችልም፡፡ የለየለት ዕብደት ካልሆነ በስተቀር፡፡

ሕወሐት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ባለመበት፣ ከማስመሰያው ‹ሕገ መንግሥት› ጀርባ ባለው ‹እውነተኛ መተዳደሪያው› (‹የተሰነይ ሰነድ› ተብሎ በሚታወቀው) ባስቀመጠው አቋሙ እስከቻለ ድረስ ኢትዮጵያውያንን እንደ ሰም አቅልጦ እንደ ገል ቀጥቅጦ ለመግዛት፤ ይህ ባይቻል ወያኔ በዚሁ ሰነድ ‹ታላቋ ትግራይ› የሚለውን ‹የትግራይ ሪፐብሊክ› የሚለውን ለመመሥረትና ኢትዮጵያን ለመበታተን በማሰብ ***‹‹ማንኛውም…ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ … እስከ መገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው፡፡››*** በማለት የመገንጠል ድንጋጌ ሕዝብ ባልመከረበትና ባላፀደቀው ‹ሕገ መንግሥቱ› ውስጥ መካተቱ የወያኔ ‹ሕገ መንግሥት› ውቅድ ከሚደረግባቸው ዐበይት ምክንያቶች አንዱ ነው፡፡ መገንጠል አገርን ምድራዊ ሲያል፣

ሕዝብን ተቅበዝባዥ እንደሚያደርግ ሩቅ ሳንሄድ ዛሬ ‹ጎረቤታችን› የሆነችው ኤርትራ ሕያው ምስክር ናት፡፡
ስለሆነም መገንጠልን በ‹መብትነት› የሚደነግግ ሕገ መንግሥት የአንድ ሉዐላዊ አገር ከፍተኛው የመተዳደሪያ ሰነድ ሊሆን አይገባም፡፡

7. የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ (አንቀጽ 40/3)

የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነትን ***‹‹የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው››*** በማለት በተግባር ለሕወሐትና አገልጋዮቹ (አገሬውን በማፈናቀል ‹ለውጭ ባለሀብት› ተብዬዎች በመቸብቸብ ጭምር) ብቻ የሥልጣንና የሀብት ምንጭ እንዲሆን በማድረግ ሕዝብና አገዛዙ ሆድና ጀርባ እንዲሆኑ ካደረጉ ዐበይት ምክንያቶች አንዱ ሲሆን፣ በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ግፍና በደል ተፈጽሟል፤ ኢፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ምክንያት ሆኗል፤በዚህ ረገድ በሚከተለውም ፖሊሲ የአካባቢና የተፈጥሮ ሚዛን እንዲዛባ ሆኗል፡፡ ይህ ድንጋጌ ጉድለቱ የተግባር ብቻ ሳይሆን ወያኔ ለራሱ ጥቅም ሲል የመሬት ሥሪት ሥርዓቱ ‹‹የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው›› የሚለው ለሕወሐትና ደጋፊዎቹ ሥልጣንና ሀብት ማደላደያ በመሆኑ ወያኔ በመቃብሬ ላይ ካልሆነ ለድርድር የሚቀርብ አይደለም ቢልም በወያኔ ግብአተ መሬት ላይ አዲስ የመሬት ሥሪት የሚያቆም ሕገ መንግሥት በሕዝብ ፍላጎት ይደነገጋል፡፡ በእኔ እምነት አዲሱ ሕገ መንግሥት ***ለኢትዮጵያውያን ዜጎች*** የመሬት ባለቤትነት መብት የሚያረጋግጥ/ዋስትና የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፡፡ በተለይም ለዘመናት በስሙ ሲነገድበት ለኖረው አርሶ አደር፡፡ በእርግጥ በሕግ የበላይነት ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ከተቻለ መንግሥት ለጋራ ጥቅም የሚያስተዳድረውና በዜጎች ባለአደራነት የሚይዘው መሬት መኖሩ ተገቢና በሌሎችም ዴሞክራሲዎች የሚሠራበት ነው፡፡
የመሬትን ሥሪት ሥርዓት በሚመለከት እ.አ.አ. ሜይ 11/2016 ‹‹ስለ መሬት ሥሪት፤ ጥቂት የውይይት መቀስቀሻ ነጥቦች›› በሚል ያቀረብኩትን ጽሑፍ መመልከትይቻላል፡፡
http://www.ethioreference.com/archives/category/amharic/page/26

8. የኢትዮጵያ የግዛት ሉዐላዊነት (አንቀጽ 2)

ወያኔ ኢትዮጵያን በዓለም ላይ ትልቋ ወደብ አልባ አገር አድርጓታል፡፡ ባንዳው ወያኔ ይህን ታላቅ አገራዊ ውሳኔ በግሉ ወስኖ ለመንግሥታቱ ማኅበር ጭምር በማሳወቅ በኢትዮጵያና ሕዝቧ ላይ ይቅር የማይባል በደል የፈጸመው ገና ከማለዳው በማስመሰያ ‹ሕገ መንግሥቱ› ‹ቋሚ አገዛዝ› ሳይመሠርት፣ በጊዜያዊነት ሳለ፣ የአገሩ ባለቤት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይፈቅድለት፣ ሥልጣኑ ሳይኖረውና በማንአለብኝነት ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ የግዛት ወሰኗ/ድንበሯ በትክክል አይታወቅም፡፡ የማስመሰያ ‹ሕገ መንግሥቱ› አንቀጽ 2 ላይ፤

***‹‹የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን የፌዴራሉን አባሎች ወሰን የሚያጠቃልል ሆኖ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የተወሰነው ነው፡፡››***

ይህ ድንጋጌ ኢትዮጵያን ‹መንግሥት አልባ› ካደረጓት መርዘኛ ድንጋጌዎች አንዱ ነው፡፡ ድንጋጌው ብዙ ጥያቄዎችን ይጋብዛል፡፡ ‹ፌዴሬሽን› አለ ወይ? አባላቱን ማን ወሰናቸው? በምን መሥፈርት ተሸነሸኑ? የክልል አጥር የተበጀለት ሕዝብ መክሮ ዘክሮ ፈቃዱን

ገልጾአል ወይ? ክልል የተባሉት የአትድረሱብኝ አጥሮች ተሠፍሮ ተለክቶ የታወቀ ድንበር አላቸው ወይ? በየትኛው ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው የኢትዮጵያ ግዛት ወሰን የተወሰነው? ለመሆኑ የትኛው አገር ነው የግዛት ወሰንን የሚያህል ዐቢይ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳይ በዚህ ውሽልሽል መልኩ የሚያስቀምጠው? ጉዳዩ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ኤርትራ ራሷን የቻለች አገር እንደመሆኗ (የኤርትራ ሕዝብ ‹ነፃነቱ› ባርነት ቢሆንበትም) ወያኔ ለኤርትራ እውቅና ሲሰጥ እንደ ሁለት ሉዐላዊ አገሮች የድንበር ወሰናቸው በሕጋዊ መልኩ አልተወሰነም፡፡ በወያኔና ሻእቢያ መካከል በ1998 ዓ.ም የተደረገውን ጦርነት ተከትሎ አሁንም በእንጥልጥል የሚገኝ ጉዳይ ነው፡፡ ሱዳንና ደቡብ ሱዳንን በሚያዋስነው ድንበራችን በኩል ያለውም ሁኔታ ልቅ መሆኑን ታዝበናል፡፡ ቢያንስ በቀደሙ የኢትዮጵያ ሕግጋተ መንግሥት እንዲሁም በሌሎች አገሮች ሕግጋተ መንግሥት ስለ ግዛት ሉዐላዊነትና ወሰን በሚናገሩ ድንጋጌዎች በሁሉም ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ***ስለ ግዛት አንድነት፣ የማይነጣጠል/የማይከፋፈል እና የማይገሰስ ስለመሆኑ በማያሻማ ቋንቋ ያስቀምጣሉ፡፡***

- የተሻሻለው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሕገ መንግሥት 1948

አንቀጽ ፩፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት በኢትዮጵያ ዘውድ ሙሉ ገዥነት ሥር የሚገኙ አገሮች ሁሉና ባሕሮቹም ደሴቶቹም ሁሉ ጭምር ነው፡፡ ሙሉ ገዥነቱና አገሮቹ ***የማይነጣጠሉ*** ናቸው፡፡ አገሮችና የገዥነት መብቶቹም ለባዕድ የማይተላለፉ ናቸው፡፡

- The Revised Constitution of the Empire of Ethiopia, 1955

***"Art. 1. The Empire of Ethiopia comprises all territories, including the islands and territorial waters, under the sovereignty of the Ethiopian Crown. Its territories and sovereignty are indivisible. Its territories and the sovereignty rights therein are inalienable."***

- የወታደራዊው መንግሥት (ደርግ) የ‹‹ኢሕዲሪ ሕገ መንግሥት›› 1980

አንቀጽ 1/2 ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ደሴቶችን ጨምሮ የየብስ፣ የአየርና የባሕር ግዛቱ የማይነጣጠልና የማይደፈር ሉዓላዊ መንግሥት ነው፡፡››

"The 1987 Constitution of the People's Democratic Republic of Ethiopia" ("Constitution" of the Military Regime/Dergue)

***Article 1/2: "The People's Democratic Republic of Ethiopia is a sovereign state whose territory comprising the land, airspace and territorial waters, including the islands, is indivisible and inviolable."***

- The Constitution of the Republic of South Africa, 1996

Article 1 "The Republic of South Africa is one, sovereign and democratic…"

- Constitution of the Federal Republic of Nigeria, 1999

Article 2/1 "Nigeria is one indivisible and indissoluble sovereign state to be known by the name of the Federal Republic of Nigeria."

- ❖ Constitution of the United Mexican States

"Article 2. The Mexican Nation is one and indivisible."

9. ጎሣን/ቋንቋን  መሠረት አድርጎ የተዋቀረው ክልል (አስተዳደራዊ ክፍፍል) (አናቅጽ 46-48)

  - የወያኔ አገዛዝ ላለፉት 25 ዓመታት ለፈጸማቸው ወንጀሎች ኹሉ እና በኢትዮጵያ ምድር በደቡብ አፍሪቃ ከነበረው የአፓርታይድ ሥርዓት ጋር ተመሳሳይነት ያለው የክልል ወህኒ ቤት ለማቋቋሙ መሠረት የሆነው ፤
  - ኢትዮጵያ እንደ አገር እንዳትቀጥል የመለያየትን መርዝ የረጨበት፤
  - ሕዝቡ ለዘመናት በደም፣ በጋብቻ፣ በበዓላት፣ በንግድ ወዘተረፈ ባደረገው መስተጋብር የገነባውን ጽኑ መተማመን ሽርሽሮ እርስ በርስ ጥርጣሬና አለመተማመን እንዲነግሥ ያደረገበት፤
  - ኢትዮጵያውያን በፈለጉበት የአገሪቱ ክፍል ተዘዋውረው የማንንም ፈቃድ ሳይጠይቁ የመኖርና የሥራ ሕይወታቸውን የመመሥረት መሠረታዊ መብት የሻረበት፤
  - ወራሪና ዘራፊ ሽፍታ መሆኑን ያስመሠከረበት፣ ለጎሣ ቆሜአለሁ እያለ የሌሎችን ጎሣ ማንነት የደፈጠጠበት፣ እፍኝ የማይሞላውን ‹ክልል›፣ አእላፋትን ደግሞ ‹ዞን፣ ወረዳ› እያለ በድንቁርና ላይ በተመሠረተ የተበላሸ አስተዳደራዊ ክፍፍል (ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑን ልብ ይሏል) አገሪቱንና ሕዝቡን ሰላም የነሳበት፣
  - የወንበዴው ‹ሥርዓት› ህልውና የተነጠለጠለበት፤

የእኩይነቱ ዋና መገለጫና የወረበሎቹ ‹ሥርዓት› የመሠረት ደንጊያ  ድንጋጌ ነው፡፡

10.የመንግሥት አወቃቀር ሥርዓት፤ አሐዳዊ ወይስ ፌዴራላዊ

የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ባህል፣ የጎሣ ስብጥር፣መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ፣ በረጅም ዘመን የማኅበረሰቡ መስተጋብር የተገነቡ የጋራ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ እሴቶች ሥርዓትን፣ ባጠቃላይ የኢትዮጵያን ልዩ ገፅታ መሠረት አድርጎ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንዲሁም ለኢትዮጵያና ሕዝቧ ዘለቄታዊ ዕድገትና ልማት የሚበጀው የመንግሥት አወቃቀርን በሚመለከት በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ምሁራን፣ የፖለቲካና ሲቪክ ማኅበራት በጥናት ላይ የተመሠረቱ አማራጮችን በንጽጽር አቅርበው፣ ሕዝቡ መክሮበት የሚወሰን እንጂ በተወሰኑ ቡድኖች ፍላጎት ሕዝብ ላይ የሚጫን ባለመሆኑ፣ አዲስ በሚረቀቀው ሕገ መንግሥት የሚታይና ለውይይት ክፍት ሊሆን የሚገባው አንኳር ጉዳይ ይመስለኛል፡፡

የመንግሥት አወቃቀር ዘላቂ ዲሞክራሲያዊ ተቋማትን ከመገንባት፣ በሦስቱ የመንግሥት የሥልጣን አካላት (ሕግ አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚ እና ሕግ አስፈጻሚ) መካከል ግልጽ ክፍፍልና የእርስ በርስ ቁጥጥርና ምዝዝን ሥርዓት ለመኖሩ ዋስትና የሚሰጥ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ወዘተ ከመኖሩ አኳያ እንጂ አንዳንዶች እንደሚሉት አሐዳዊ መሆኑ የቀድሞ ሥርዓት ናፋቂነት፣ ያልተማከለ ፌዴራላዊ መሆኑ ደግሞ ለእኩልነትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋስትና አይደለም፡፡ እንደ ወያኔ ‹ፌዴራላዊ› ብሎ ፈላጭ ቆራጭ አሐዳዊነትም አለና፡

ምርጫው አሐዳዊም ሆነ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊነቱን ለማረጋገጥ በሕገ መንግሥት ደረጃ ሊመለከቱ የሚገባቸው ዋስትናዎች በግልጽ መደንገግ ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይም በማዕከላዊ/ፌዴራል መንግሥቱ እና በአካባቢያው አስተዳደሮች/በፌዴሬሽኑ አባል ግዛቶች መካከል የሚኖረው የሥልጣን ክፍፍልና አንዱ በሌላው የሥልጣን ክልል ውስጥ ጣልቃ በመግባት ግጭት ሲፈጠር ግጭቱ የሚፈታበትን መንገድ በግልጽ ማስቀመጥን ይጠይቃል፡፡

11.ቅርፀ መንግሥት፤ፓርላሜንታዊ ወይስ ፕሬዚዳንታዊ

እንደ መንግሥት አወቃቀር ሥርዓቱ የቅርፀ መንግሥት ጉዳይም ለውይይት ክፍት መሆኑ እንተጠበቀ ሆኖ ፣ በጥናት ላይ የተመሠረቱ አማራጮች እና የአማራጮቹ ጥቅምና ጉዳት በንጽጽር ቀርቦ በሕዝብ ተሳትፎ መወሰን ያለበት ይመስለኛል፡፡

12. ጎሣን መሠረት ያደረግ የፖለቲካ ማኅበር ማቋቋም

አሁን ባለው ‹የመንግሥት› አወቃቀር ሥርዓት የአስተዳደራዊ ግዛቶች ክፍፍል ጎሣን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ለሥልጣን የሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀትም በአብዛኛው ጎሣ ላይ እንደሆነ ይታያል፡፡ ከዚህ ቀደም ባቀረብኳቸው አስተያየቶች ደጋግሜ እንደገለጽኩት ይህ አደረጃጀት ለአገር ህልውናና ለሕዝብ አብሮነት ጠንቅ ነው፡፡ ከአድልኦና ዘረፋ አንሥቶ ጎሣን መሠረት እስካደረገ የጅምላ ጭፍጨፋ እንደሚሄድ የወንበዴው ሕወሐት ሥርዓት ለዚህ ሕያው ማስረጃ ነውና፡፡ በዚህም ምክንያት አዲስ በሚረቀቀው ሕገ መንግሥት ጎሣን መሠረት ያደረገ የፖለቲካ አደረጃጀት የሚያግድ ድንጋጌ ማስገባት ተገቢ ይሆናል፡፡

ለማጠቃለል ወንበዴው ሕወሐት ላለፉት 25 ዓመታት ኢትዮጵያን ሲገዛ የቆየው በሕገ መንግሥት ሳይሆን በደደብ በረኻ አዘጋጅቶ ያመጣውን የሕወሐት አጀንዳ (የጫካ ሕግ) በማስመሰያ ‹ሕገ መንግሥቱ› ሥርዋጽ በማስገባት ነው፡፡

በዚህ ጽሑፍ ለማመልከት እንደተሞከረው የወያኔ ‹ሕግ መንግሥት›ን በአዲስ የመተካቱ አስፈላጊነት ተግባራዊ ባለመሆኑ ብቻ ሳይሆን በዋናነት ከአገር አንድነትና ከግዛት ሉዐላዊነት፣ ከመንግሥት አወቃቀር፣ ከሕግ የበላይነት፣ ለሥልጣን ገደብ ከማበጀት፣ ከዳኝነት ነፃነት፣ ከመሬት ሥሪት ሥርዓት፣ ከፖለቲካ ፓርቲ አደረጃጀት፣ ወዘተረፈ አኳያ ሕገ መንግሥታዊ መርሆችን ያልተከተለና ዴሞክራሲያዊ ባለመሆኑ ነው፡፡ ለወደፊቱ የሚዘጋጀው ሕገ መንግሥት የአገር አንድነትን፣ ብሔራዊ ማንነትን፤ ሁላችን የምናጋራቸውን መልካም አገራዊ እሤቶችን ማንፀባረቅን፣ ለጋራ ልማትና አብሮ ለማደግ ጥሩ መደላድል መፍጠርን... ታሳቢ ቢያደርግ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ይበጃል የሚል እምነት አለኝ፡፡ እዚህ የቀረቡት ጉድለቶችና በወደፊቱ ሕገ መንግሥት እንዲካተቱ የተሠነዘሩት ነጥቦች ባሕሩን በማንካ ስለሚሆን ኹሉም በጎ የሚለውን በመጨመር ሊያዳብረው ይገባል፡፡ በተለይም በጣም የማከብራቸውና ስለ ወንበዴው የሕወሐት ቡድን እኩይ ተግባራት በተባ ብእራቸው ሳይታክቱ ለኢትዮጵያውያንና ለዓለም እያጋለጡ ያሉት፣ የሕገ መንግሥት ሕግ ሊቅ ጋሼ (ፕሮፌሰር) አለማየሁ ገብረ ማርያም በዚህ ርእስ ጉዳይ ላይ የጠመመውን አቅንተው የጎደለውን ሞልተው በሥፋት ጽሑፍ እንደሚያቀርቡበት እተማመናለሁ፡፡

ከልሂቅ እስከ ደቂቅ በውስጥም በውጭ ያለን ኢትዮጵያውያን መሪር አገዛዝ ያፀናብንን የሕወሐትና አገልጋዮቹን ቆሻሻ ሥርዓት በኅብረት በማስወገድ በእኩልነት ላይ የምትመሠረት አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት እግዚአብሔር ይርዳን።